ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ ሙስና

ቅፅ 02 ቁጥር 1

ነሀሴ 15 /2016/ ዓ.ም

በውስጥ ገፆች

አንዳንድ የፖሊስ አመራርና አባላት ላይ የሚስተዋሉ የሥነምግባር ግድፈቶችን ማረም ያስፈልጋል

ገጽ 4

በተቋማት ላይ የሚስተዋለውን በተቋማት ላይ የሚስተዋለውን ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መታገል

ገጽ 2

## ሙስና እና ብልሹ አሰራር የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርም ትግበራ ላይ እንቅፋት እንዳይፈጥር በልዩ ትኩረት ይሰራል - ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር)



የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ በኢትዮጵያ ሙስና እና ብልሹ አሰራር አገርና ሕዝብን በከፍተኛ ደረጃ እየጎዱ መሆኑን ተናግረዋል:: ይህንንም ከግምት በማስገባት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በአገርዓቀፍ ደረጃ የፀረ-ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ ተቋቁሞ እየተሰራ መሆኑን ነው ያነሱት:: በተለይም ሙስናን አገራዊ ችግር አድርጎ በመውሰድ በተቀናጀ መንገድ አጀንዳውን ከመምራትና መፍትሄ ከማምጣት አኳያ ጅምር ሥራዎች መከናወናቸውን ጠቅሰዋል::

ያም ሆኖ የተቋማት አቅም አለመዳበርና የሕዝብ ግንዛቤ በሚፈለገው ልክ አለመጎልበቱ የፀረ-ሙስና ትግሉ የሚፈለገውን ውጤት እንዳያመጣ እንቅፋት መሆኑን ገልጸዋል:: በተለይም የፀረ-ሙስና ትግሉን የሚያስተባብሩ ተቋማት ጠንካራ የሪፎርም ሥራ በመሥራት ነጻና ገለልተኛ ሆነው ተጠያቂነትን እስከማረጋገጥ የሚደርስ ሥራ ሊሰሩ እንደሚገባ ተናግረዋል::

ወደ ገጽ 4 ዞሯል..

## በ2017 በጀት ዓመት ብልሹ አሰራርን መከላከል ዋነኛው የመንግሥት ዐቢይ ጉዳይ ነው - ም/ጠ/ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ





ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ ይህን ያሉት ለጠቅላይ ሚንስትሩ ተጠሪ የሆኑ አስፈጻሚ አካላት የ2016 በጀት አመት አፈፃፀም እና የ2017 ዕቅድን ግምገማ ባካሄዱበት ወቅት ነው:: በሪፖርቱ ከቀረቡ ጉዳዮች ውስጥ መልካም ውጤቶችን ማጠናከር፣ የታዩ ክፍተቶችን ማረምና ጠንካራ አፈጻጸሞችን ማስቀጠል እንደሚገባ አቅጣጫ አስቀምጠናል ብለዋል:: ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ አክለውም ቁልፍ ችግሮችን የሚፈታ፣ ሙስናን መዋጋት የሚችል አመራር ለመገንባት የሁሉንም ትኩረት እንደሚፈልግ ጠቁመዋል:: በአዲሱ በጀት ዓመት መልካም አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥን በመሰረታዊነት ለመቀየር መንግሥት ትኩረት መስጠቱን ጠቅሰው፥ ተቋማቱም ለስኬቱ እንዲረባረቡ አሳስበዋል:: ብልሹ አሰራርን መከላከልም ዋነኛው የመንግሥት ዐቢይ ጉዳይ ነው ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፥ ተቋምን ማዘመንና ዘላቂነትን ማረጋገጥ ይገባል ብለዋል::

የተቋማቱ ዕቅድና ሪፖርት ከአገራዊ ስትራቴጂክ ዕቅድና ከልማት ግቦች ጋር በተናበበ መልኩ የተዘጋጁ፣ መፈጸም የሚችሉና የሚለኩ መሆን እንዳለባቸውም አሳስበዋል:: በመድረኩ የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) የኮሚሽኑን የ2016 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ሪፖርት እና የ2017 በጀት ዓመት እቅድ አቅርበው ውይይት ተደርጎበታል::

# በተቋማት ላይ የሚስተዋለውን ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መታገል ይገባል - ርዕሰ መስተዳድር እንዳሻው ጣሰው





የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ እንዳሻው ጣሰው በመስተዳድር ምክር ቤቱ ስብሰባ 18ኛ መደበኛ ስብሰባ መድረክ ማጠቃለያ ላይ በሰጡት የስራ መመሪያ እንደገለጹት በክልሉ የአገልግሎት አሰጣጥን በማዘመን ለላቀ የህዝብ ተጠቃሚነት መስራት ይገባል ብለዋል። አመራሩ የተሰጠውን ጊዜ በአግባቡ በመጠቀም ስራውን በውጤታማነት ማሳካት እንደሚገባም ገልፀዋል።

በተቋማት የሚስተዋለውን ብልሹ አሰራር መታገል ይገባል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፣ ሌብነት፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች እና ሌሎች መሰል የአሰራር ማነቆዎችን መፍታት እንደሚገባም አስረድተዋል።

በመድረኩ የመስተዳድር ምክር ቤቱ አባላት ከርዕሰ መስተዳድር አቶ እንዳሻው ጣሰው ጋር የግብ ስምምነት ተፈራርመዋል።

## የልማትና የመልካም አስተዳደር ማነቆ የሆኑትን ሌብነትንና ብልሹ አሰራርን በመታገል የክልሉን ህዝብ ከተረጂነት አስተሳሰብ ለማላቀቅ በትኩረት እንሰራለን - ወ/ሮ ዓለሚቱ ኡሞድ

በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ሆነው የተሾሙት ወ/ሮ ዓለሚቱ ኡሞድ በጉባዔው ላይ ባስተላለፉት መልእክት፤ በክልሉ ያለውን ሰፊ የተፈጥሮ ሀብት በማልማት በህዝቡ ለሚነሱ የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በትኩረት ይሰራል።

ወ/ሮ ዓለሚቱ ኡሞድ አክለውም የልማትና የመልካም አስተዳደር ማነቆ የሆኑትን ሌብነትንና ብልሹ አሰራርን በመታገል የክልሉን ህዝብ ከተረጂነት አስተሳሰብ ለማላቀቅ በትኩረት እንሰራለን ብለዋል። የክልሉ ምክር ቤት አባላት ለልማት እቅዶች ተግባራዊነት የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን አጠናክረው እንዲቀጥሉም ጠይቀዋል።






## በክልሉ የሌብነትና ብልሹ አሰራር ትግል ይበልጥ በማጠናከር የተጠያቂነት ስርዓቱን የማስፈን ስራ በልዩ ትኩረት ይሰራል - አቶ ኦርዲን በድሪ

የሀረሪ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኦርዲን በድሪ በክልሉ በ2017 በጀት ዓመት የሌብነትና ብልሹ አሰራር ትግል ይበልጥ በማጠናከር የተጠያቂነት ስርዓቱን የማስፈን ስራ በልዩ ትኩረት እንደሚሰራ ገልፀዋል።

በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች እንዲሁም በሰው ተኮር ተግባራት ላይም በልዩ ትኩረት የሚሰራ መሆኑን አመላክተዋል። እንዲሁም ህገወጥ ግንባታና የመሬት ወረራ ላይ ሕግ ማስከበር ስራ ይሰራል ብለዋል።



የብልሹ አሰራርና ሌብነት ትግል ይበልጥ በማጠናከር የተጠያቂነት ስርዓቱን የማስፈን ስራ በልዩ ትኩረት እንደሚሰራም ጠቁመዋል። ህብረተሰቡ የሚያነሳቸው የአገልግሎት አሰጣጥና የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲሁም ብልሹ አሰራር ለመፍታትና ለማረም የተለያዩ የሪፎርም ተግባራት ይከናወናል። በሸቀጦች ላይ ተገቢ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪ በሚያደርጉ አካላት ላይ የክትትልና ቁጥጥር ስራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ገልፀዋል።

# በ2017 በጀት ዓመት በመዲናዋ ሌብነትና ብልሹ አሰራርን በመዋጋት የተቀላጠፈ አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ ላይ በትኩረት ይሰራል- ከንቲባ አዳነች አቤቤ





የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የ2016 በጀት ዓመት የመንግስትና የፓርቲ ስራ አፈፃጸም ግምገማ እና የ2017 በጀት ዓመት የዕቅድ ዝግጅት በዓድዋ መታሰቢያ ውይይት ተካሄዷል፡፡ በዚሁ ጊዜ የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደገለፁት በ2016 በጀት ዓመት በዕቅድ የተያዙ የልማት ተግባራት በስኬት በመምራት ቃልን በተግባር መፈጸም ያስቻሉ ስኬታማ የልማት ተግባራት ማከናወን ተችሏል ብለዋል፡፡ ፍትሃዊና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ በ10 ተቋማት ጠንካራ ሪፎርሞች እና አሰራሮችን የዘረጋንበት ነበር ብለዋል፡፡ በመዲናዋ የዜጎችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ያስቻሉ ስኬታማ የልማት ተግባራትን ማከናወን ቢቻልም በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮች እንዳሉም አመላክተዋል፡፡ እንዲሁም ከህዝብ ጋር ባደረግናቸው በርካታ ውይይቶች የተለዩ ችግሮችን በተለይም ሌብነት፣ ጉቦኝነት እና ብልሹ አሰራር ላይ ትኩረት አድርገን እንሰራለን ብለዋል፡፡ የስኬት ምንጭ የሆኑ ተግባራትን በተሞክሮ በመውሰድ በ2017 በጀት ዓመት የተሻለ ስራ እንደሚሰራ አመላክተዋል፡፡ በተለይ ሌብነትን ብልሹ አሰራርን ብሎም በአገልግሎት አሰጣጥ እና በመልካም አስተዳደር ላይ የሚታዩ ችግሮችን መቅረፍ እንደሚገባ አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል፡፡

# በ2017 በጀት አመት መልካም አስተዳደርን በማስፈንና ብልሹ አሰራርን በማስቀረት የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሰራ ተገለፀ

የሀረሪ ክልል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ቢሮ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመፍታት የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት እየተከናወኑ በሚገኙ ተግባራት ላይ አጠቃላይ ግምገማ አካሄዷል፡፡

በግምገማው ላይ በዘጠኙም ወረዳዎች ላይ ተመድበው እየሰሩ ያሉ አቃቤ ህጎችና የቢሮው 12 ዳይሬክተሮች እየተሳተፉ መሆኑን የገለፁት የቢሮው ምክትል ኃላፊ ኮሚሽነር ለታ በዳዳ፥ በቀጣይ በዘርፉ የሚሰጠውን አገልግሎት የተሻለ ከማድረግ አንፃር ግምገማው ትልቅ ፋይዳ ያለው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የግምገማው ተሳታፊዎች በበኩላቸው የተለያዩ ሀሳቦችን በጥልቀት ያነሱ ሲሆን፥ በዚህ መልኩ ጠንከር ያለ ግምገማ መካሄዱ በሚገባ እራሳቸውን በማወቅ ክፍተቶችን ለመሙላት ትልቅ ፋይዳ ያለው ነው ብለዋል፡፡ በግምገማው ላይ የሚነሱትን ሀሳቦች በተለይ ሙስና እና ብልሹ አሰራር እንዲሁም የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ከማስቀረት አንፃር እንደ ትልቅ ግብዓት የሚጠቀሙበት መሆኑን አመላክተዋል፡፡



የሀረሪ ክልል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ቢሮ ም/ኃላፊ ኮሚሽነር ለታ በዳዳ

## ከገጽ አንድ የዞረ...

የትምህርት፣ የባህልና የእምነት ተቋማት እንዲሁም መገናኛ ብዙኃን ትውልድን በመልካም ስብዕና በመገንባት የፀረ-ሙስና ትግሉን በመደገፍ ረገድም ሚናቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል::

የፀረ-ሙስና መታገያ ሥልቶች የሆኑት የግንዛቤ ማስጨበጥ፣ የመከላከልና የሕግ ማስከበር ሥራዎች እኩል ተግባራዊ አለመሆናቸው ለተጀመረው የፀረ-ሙስና ትግል ተግዳሮት መሆኑን ጠቅሰዋል:: በተለይም ቀደም ሲል የነበሩ የሕግ ማዕቀፎች ጠንካራ አለመሆን ሰዎች አስልተው ሙስና እንዲፈጽሙ የሚያደርጉ መሆናቸውን ጠቅሰው፥ ይህም የሙስና መከላከል ሥራው ላይ ጫና አሳድሯል ብለዋል:: በዚህ ረገድ የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጁ ፀድቆ ተግባራዊ ሲሆን የፀረ-ሙስና ትግሉን ውጤታማ እንደሚያደርገው ተናግረዋል::

በተያዘው 2017 በጀት ዓመት በመንግሥት ተቋማት የሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቅረፍ በልዩ ትኩረት እንደሚሰራ ገልፀዋል:: መንግሥት ተግባራዊ ማድረግ የጀመረው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በመልካም አስተዳደር ችግርና በሙስና እንዳይደናቀፍ የተቀናጀ ርብርብ እንደሚደረግም ተናግረዋል:: በዚህም የመንግሥት ኃብት በሙስና እና ብልሹ አሰራር እንዳይባክን ይደረጋል ነው ያሉት::

መንግሥት የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲቀረፉና አገልግሎቶች ከሙስና በጸዳ አግባብ እንዲሰጡ ከምን ጊዜውም በላይ በትኩረት እንደሚሰራ አረጋግጠዋል:: ሕዝቡም ከመንግሥት ጎን በመቆም አገርና ሕዝብን ወደ ኋላ የሚጎትተውን ሙስና በተሟላ መልኩ በመታገል የአገሪቱን እድገት ለማስቀጠል የበኩሉን እንዲወጣ ጠይቀዋል::

# በአንዳንድ የፖሊስ አመራርና አባላት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችንና የሥነምግባር ግድፈቶችን በማረም አገልግሎት መስጠት ይጠበቅብናል

## - ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ





ፖሊስ መልካም ሥነምግባር ተላብሶ ለኅብረተሰቡ አገልግሎት እንዲሰጥና አገልግሎቱን የበለጠ ለማዘመን በሚያስችል ሠነድ ላይ የፌደራል ፖሊስና የአዲስ አበበ ፖሊስ ከፍተኛ አመራሮች ውይይት አካሄደዋል:: በዚሁ ወቅት የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ ገ/ሚካኤል እንደገለጹት፣ የኢትዮጵያን የፖሊስ አገልግሎት የበለጠ ለማዘመን በከፍተኛ ተነሳሽነት እየተሰራ ነው::

በፖሊስ አገልግሎት ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው በፌደራል ፖሊስ የዜጎች ተሳትፎ መተግበሪያን በመጠቀም ቅሬታውን እንዲያቀርብም የፌዴራል ፖሊስ ጥሪ አቅርቧል::በተጨማሪም በአንዳንድ የፖሊስ አመራርና አባላት ላይ የሚስተዋሉ የሥነምግባር ጉድለቶችን ለማረም በሚደረገው ከፍተኛ ጥረት ውስጥ ኅብረተሰቡ ድጋፉን አጠናክሮ የድርሻውን እንዲወጣም ጥሪ መቅረቡን ከፌደራል ፖሊስ የተገኘው መራጃ ያመላክታል:: ከፍተኛ አመራሮቹ በፖሊስ ውስጥ የሚስተዋሉ አንዳንድ የሥነምግባር ጉድለቶችና ብልሹ አሠራሮችን በፍጥነት በማረም ለኅብረተሰቡ ፈጣንና ፍትሃዊ አገልግሎት ለመስጠት ስምምነት ላይ ደርሰዋል ተብሏል::



በተያያዘ መረጃ በተጠናቀቀው የ2016 በጀት ዓመት በታክስ ሥወራ፣ በግብር ማጭበርበር፣ ያለደረሰኝ ግብይት በመፈጸምና ሐሰተኛ ማስረጃ ከመጠቀም ጋር ተያይዞ ከ5 ሺህ በላይ መዝገቦች ለዐቃቤ ሕግ መተላለፋቸውን የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ምክትል ኮሚሽነር ጄኔራልና የወንጀል ምርመራ ቢሮ ኃላፊ ዘላለም መንግሥቴ ገልፀዋል:: በአገርና ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ወንጀሎችን በመመርመር ተገቢው የሕግ እርምጃ እንዲወሰድ የማድረግ ሥራ በትኩረት እየተከናወነ መሆኑንም ተናግረዋል::

ለአብነትም በአፍሪካ ኅብረት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ከፍተኛ መጠን ያለው አሜሪካን ዶላር ለማውጣት የነበረውን ሙከራ በማክሸፍ የምርመራ ሂደቱን በማጠናቀቅ ተጠርጣሪዎች ማረሚያ ቤት ወርደው ጉዳያቸውን እየተከታተሉ መሆኑን አንስተዋል:: በአገር ኢኮኖሚ ላይ የሚፈጸሙ አሻጥሮችን በመቆጣጠር ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑን ጠቅሰው፣ ለአብነትም ከ25 ቢሊየን ብር በላይ በመንግሥትና በሕዝብ ኃብት ላይ ጉዳት ያደረሱ ሰዎች በቁጥጥር ሥር ውለው ምርመራቸው እየተጣራ መሆኑን ገልጸዋል::

በድምሩም ከ5 ሺህ በላይ መዝገቦች ምርመራቸው ተጠናቆ ለዐቃቤ ሕግ መተላለፋቸውን ነው ያስረዱት:: በአገር ኢኮኖሚ ላይ አሻጥር ለመፈጸም ሁኔታውን እየቀያየረ የሚገኘውን የወንጀል ተግባር ለመቆጣጠር ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በመተባበር በዕውቀትና ቴክኖሎጂ የተመሰረተ ሥራ እየተሰራ ነው ብለዋል:: መንግሥት በተለያየ ሁኔታ የተወጠረ የሚመስላቸው አካላት ትክክለኛ የሚመስል ሐሰተኛ ማስረጃን በማዘጋጀት በኮንቴነር ጭምር ምርትን ወደ አገር ቤት ለማስገባት የሞከሩ አካላት መኖራቸውን ገልጸዋል::

በሌለ የንግድ ድርጅት ሐሰተኛ መታወቂያና የንግድ ሥርዓት መስፈርቶችን በመጠቀም በአገር ኢኮኖሚ አሻጥረኞች ላይ በፎረንሲክ ምርመራ በማጣራት ወንጀሉን የመከላከል ሥራ መሰራቱን ተናግረዋል:: ሕዝብና መንግሥት የሰጣቸውን አደራ ወደጎን በመተው በሌብነት ተግባር በተሰማሩ የመንግሥትና የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሥራ ኃላፊዎችም ተጠያቂ የማድረግ ሥራ እየተሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል::

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚቀርቡ የተቋማት ኦዲት ሪፖርት ጉድለቶችን መነሻ በማድረግ የሕዝብና መንግሥት ኃብትን ላልተገባ ዓላማ ባዋሉ የሥራ ኃላፊዎችንም ተጠያቂ የማድረጉ ሥራ ተጠናክሮ ቀጥሏል ብለዋል:: በቀጣይም የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስን በዕውቀትና ቴክኖሎጂ የሚመራ አስተማማኝ ተቋም በማድረግ ወንጀልን የመከላከል፣ የሰላምና ደኅንነት በማስጠበቅ ፍትሕ የማረጋገጥ ኃላፊነቱን በብቃት ለመወጣት ተከታታይ ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝ ተናግረዋል::

# የኮሚሽኑ አመራርና ሠራተኞች የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር አካሄዱ






ሙስና ኮሚሽን አመራርና ሠራተኞች በአዲስ አበባ የካ ክፍለ ከተማ ፈረንሳይ ጉራራ አካባቢ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር አካሄደዋል። የዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በሀገር አቀፍ ደረጃ "የምትተክል አገር፥ የሚያፀና ትውልድ" በሚል መሪ ሀሳብ በአገርዓቀፍ ደረጃ እየተካሄደ ይገኛል።

በቀጣይም ነሐሴ 17 ቀን 2016 ዓ.ም በአገርዓቀፍ በአንድ ጀምበር 600 ሚሊዮን ችግኞችን የመትከል ንቅናቄ ላይ በመሳተፍ አሻራችንን እንደምናኖር ይጠበቃል።

# አሜሪካዊው ሴናተር ቦብ ሚኒንዴዝ በኢትዮጵያ ላይ ጫና እንዲደረግ ከግብጽ ጉቦ በመቀበላቸው ጥፋተኛ ተባሉ



በቀጣዩ ህዳር ወር በሚካሄዳው የአሜርካ ምርጫ እንደማይሳተፉ እየተነገረ ነው፡ ፡ በኢትዮጵያ ላይ ጫና ለመፍጠር እንዲያስችላቸው በኒውጀርሲ በንግድ ስራ ላይ ከተሰማሩ 3 የግብጽ ሰዎች እጅ ወርቅና ጥሬ ገንዘብ ጉቦ ፡ ይህም ሴናተሩ ራሳቸውን ለግብጽ መንግሥት ወኪል አድርገው በመቆም ሰርተዋል የሚል ክስ ሲቀርብባቸው ነበር።

ሴናተር ቦብ ሚኒንዴዝ በዘረፋ፣ ጉቦ በመቀበል፣ ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም፣ በሴራ፣ ፍትህን በማደናቀፍና መሰል 16 ወንጀሎች ተሳትፎ አድርገዋል በሚል ተጠርጥረው ክስ የተመሰረተባቸው መሆኑንም ተመላክቷል።

በመሆኑም በሚቀጥለው ህዳር ወር በሚካሄደው የአሜርካ ምርጫ ዴሞክራቶችን ወክለው የሚወዳደሩት ቦብ ሜኒዴዝ ስልጣናቸውን በገዛ ፈቃዳቸው እንዲለቁ ጥሪ የተደረገላቸው ሲሆን፣ በሌላ እጩ እንደሚተኩም ነው የተገለጸው።

የ70 ዓመት አዛውንቱ ቦብ ሚኒንዴዝ ስልጣናቸውን መከታ በማድረግ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዶላሮችን ከሀገሪቱ ወታደራዊ እርዳታ ለመውሰድ አመቻችተዋልም ተብለዋል። አጋሮቻቸውን ከወንጀል በመከላከል፣ አለአግባብ እንዲበለጽጉ በባለቤታቸው በኩል ከግብጽ የደህንነት ሰዎች ጋር ግኑኝነት በመፍጠር ስልጣንን አላግባብ ተጠቅመዋል ሲል አቃቤ ህግ ክስ መስርቶባቸዋል።

የውጭ ጉዳይ ግኑኝነት ቋሚ ኮሚቴ ሊቀ-መንበር ሆነው ስራቸውን እየሰሩ ስለመሆናቸው የሚናገሩት ቦብ ሚኒንዴዝ፣ በተጠረጠሩበት ወንጀል ለ9 ሳምንታት ምርመራ ሲደረግባቸው ቢቆይም አልፈጸምኩም እያሉ ይገኛሉ፡ ፡ ሴናተሩ "እኔ በህዝብ ፊት የገባሁትን ቃል አልጣስኩም።

ለማንም ሀገር የምሰራው ጉዳይ የለኝም" ብለዋል። አሜርካዊው ሴናተር በተጠረጠሩበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ የማምሻ እድሜያቸውን አስርት ዓመታት ወደ ማረሚያ ቤት ሊያመሩ እንደሚችሉ አሶሼትድ ፕሬስ ዘግቧል።

# ኮሚሽኑ ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ጋር በቅንጅት በሰራቸው ተግባራት እውቅና ማግኘቱን ገለፀ





የአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2016 በጀት አመት ባከናወናቸው የትውልድ ሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ሥራዎች ከከተማው ትምህርት ቢሮ እውቅና ማግኘቱን ገልጿል። ኮሚሽኑ ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ጋር በ2016 በጀት አመት በቅንጅት በሰራቸው ተግባራት በተለይ በትምህርት ቤቶች ክበባትን በማደራጀት፣ በማጠናከርና ቀጣይነት ያለው የትውልድ ሥነምግባር ቀረፃ ስራዎች እንዲሰሩ አድርጓል።

እንዲሁም በሥነምግባራቸው ምስጉን የሆኑ ሞዴል ተማሪዎችንም እውቅና የመስጠትና የማበረታታት ስራዎች መሰራቱም ተመላክቷል። ኮሚሽኑ በቀጣዩ የ2017 በጀት አመት ከቢሮው ጋር በትውልድ የሥነምግባር ግንባታ ላይ የሚሰራበትን የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሟል።

# የመልካም አስተዳደርና የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ከሙስና እና ብልሹ አሠራር የፀዳ እንዲሆን በጋራ መስራት አለብን - 

## ኮሚሽነር ሙሉሠው ዘውዴ





የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራር እና ሠራተኞች መልካም አስተዳደርን በማስፈንና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ሰው ተኮር አገልግሎቶችን ከማሳለጥ ረገድ መሰራት በሚችሉባቸው ጉዳዮች ላይ ውይይት ማድረጋቸው ተገልጿል።

የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ሙሉሠው ዘውዴ እንደገለፁት የአገልግሎት አሰጣጥንና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየትና በመፍታት ከሙስና እና ብልሹ አሠራር የፀዳና ሠው ተኮር በሆነ መልኩ መስራት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

የተዘጋጀው ዕቅድ ከአሠራርና ከአደረጃጀት አኳያ አስራ አንድ ችግሮች ተለይተው የተቀመጡ መሆኑን ገልፀው፥ የተለዩ ችግሮችን በየጊዜው እየገመገምን መፍታት ይኖርብናል ብለዋል። የኮሚሽኑ ም/ኮሚሽነር ዳግም ዳንኤል በበኩላቸው የተቀመጠው ዕቅድ ምላሽ የሚገኝበትን የድርጊት መርሃግብር መሠረት በማድረግ አሠራራችን እየገመገምን ወቅቱን የሚመጥንና ለአፈፃፀም ምቹ የሆኑ አደረጃጀቶችን በመዘርጋት የመረጃ ጥራትና ተደራሽነት ላይ ትኩረት አድርገን መስራት እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል። በ2016 በጀት ዓመት ያገኘናቸውን መልካም ተሞክሮዎች በመውሰድ በቀጣዩ በጀት ዓመት ቅንጅታዊ አሰራሮችን በማጠናከር ችግሮችን በዘላቂነት የምንፈታበትና የአጭር ጊዜ መፍትሔ የሚሹ ተግባራትንም እየለየን የምንሰራ ይሆናል ብለዋል።

የኮሚሽኑ ም/ኮሚሽነር ታደሠ አይበራ በበኩላቸው ኮሚሽኑ ያሉትን ግብዓቶች በአግባቡ ከመያዝና ከመጠቀም አኳያ የዕቅዱን ተገቢነት በመለየት፣ በምንሰራቸው ጉዳዮች ላይ አቅጣጫዎችን በመከተልና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየት መስራት እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል። በኮሚሽኑ የልማት ዕቅድ ዳይሬክቶር አቶ መሳይ አልታዬ የውስጥና የውጭ የመልካም አስተዳደርና ብልሹ አሠራር ችግሮችን ለመፍታት በተለዩ ነጥቦች ላይ የተዘጋጀ ሰነድ ቀርቦ ውይይት መደረጉ ተገልጿል።

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

በፌደራል የሥነምግባር እና
የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየሁለት ሳምንቱ
የሚዘጋጅ ዲጂታል
ጋዜጣ

| | |
|---|---|
| ስልክ | 011552-77-79 |
| ፖ.ሳ.ቁ | 34799 |
| ኢ-ሜይል | FeaccEthiopia2013@et |
| ድረ-ገጽ | www.feacc.gov.et |
| ፌስቡክ | www.facebook.com/feaccOfficial |
| ቴሌግራም | t.me/feacc |
| ትዊተር | www.twitter.com/EthiopiaFeacc |
| ዩቲዩብ | Federal Ethics & Anti-Corruption Commission |

ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች
www.feaccdars.gov.et

ለፌደራል የሥነምግባር
እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
የሙስና ወንጀል ጥቆማ
መስጫ አድራሻዎች

| | |
|---|---|
| ስልክ | 011552 77-92/ 011553-38-52 |
| ሞባይል | 0935947533 |
| ፖ.ሳ.ቁ | 34799 |
| ድረ-ገጽ | www.feacc.gov.et |
| ኢ-ሜይል | CorruptionReportEthiopia@feacc. gov.et |
| ቴሌግራም | t.me/CorruptionPointing |
| ዋትስኣፕ | wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1 |

# ርዕሰ-አንቀፅ

## አገርዓቀፍ የኮሚሽኖች የአቻ ለአቻ ድጋፋዊ ሱፐርቪዥን ፕሮግራም ቀጣይነት ሊኖረው ይገባል!

አገርዓቀፍ የኮሚሽኖች የአቻ ለአቻ ድጋፋዊ ሱፐርቪዥን ፕሮግራም በፌደራል፣ በክልል እና በከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ተካሄዷል፡፡ ድጋፋዊ ሱፐርቪዥኑ በዋናነት በ2016 በጀት ዓመት አገርዓቀፍ ኮሚሽኖች ያከናወኗቸውን የሥነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ሥራዎች እንዲሁም በ2017 በጀት ዓመት የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ በተለይም በ2016 በጀት ዓመት የሥነምግባር አቅም ግንባታ ሥልጠና፣ በፀረ-ሙስና ትግል የሕዝብ ግንዛቤ ማጎልበቻ፣ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን አደረጃጀት እና አሰራር የማጠናከር እና የሙስና መከላከል ጥናትና ክትትል እንዲሁም የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራዎች ላይ አትኩሯል፡፡

በተጨማሪም በሀብት ማሳወቅና ምዝገባ፣ የመረጃ ትንተና እና ምክረ-ሐሳብ የማመንጨት፣ የሀብት ምንጭ መረጃ ትክክለኛነት የማጣራትና ተጠያቂነት የማረጋገጥ፣ የሙስና መረጃ ጥቆማ ቅበላ እና ትንተና እንዲሁም የኮሚሽኑን ተቋማዊ አቅምና ብቃት ማሻሻያ ሥራዎች አፈጻጸምም ተዳሷል፡፡ ኮሚሽኖች አገራዊ ተልዕኳቸውን እንዲወጡ ለማድረግ ነጻ፣ ገለልተኛ እና ብቃት ያላቸው ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣ በሱፐርቪዥን ጊዜ ተቋማዊ አቅማቸውን መፈተሹ በትኩረት አቅጣጫው ውስጥ ተካተዋል፡፡

በሱፐርቪዥኑ ዜጎች በፀረ-ሙስና ተቋማት ያላቸውን እምነት የሚያሳድጉ ጠንካራ የሪፎርም ሥራዎችን ጭምር ለማከናወን ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎች ከተለያዩ አካላት ተሰብስቧል፡፡ እንዲሁም የ2016 በጀት ዓመት የኮሚሽኖች ሥራዎችን በተመለከተ የታዩ ጥንካሬዎች፣ ጉድለቶች፣ ተሞክሮዎች፣ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ ከሐምሌ 20-30/2016 ዓ.ም በፌደራል፣ በክልል እና ከተማ አስተዳደር ኮሚሽኖች አቻ ለአቻ የድጋፋዊ ሱፐርቪዥን ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡

በአገርዓቀፍ ኮሚሽኖች የተካሄደው የአቻ ለአቻ ድጋፋዊ ሱፐርቪዥን ፕሮግራም መረጃዎችን መለዋወጥ ብቻ ሳይሆን ተቋማት ላይ ግልፅነት እና ተጠያቂነትን አጉልቶ አሳይቷል፡፡ ፕሮግራሙ በዋናነት ጠንካራ ጎኖችን በማስቀጠልና የታዩ ክፍተቶችን ደግሞ በመሙላት የኮሚሽኖችን ተቋማዊ አቅም በማጎልበትና በሀገር አቀፍ ደረጃ ትስስር ፈጥሯል፡፡ ይህን አይነቱ አሰራር እንደ መልካም ተሞክሮ የሚወሰድበት ከመሆኑ ባለፈ፣ እውቀት ላይ የተመሠረተ ግንዛቤ የሚያስገኝ በመሆኑ በቀጣይም ሌሎች ዘርፎች እንደተሞክሮ ሊወስዱት ይገባል፡፡

በአገርዓቀፍ ኮሚሽኖች የአቻ ለአቻ ድጋፋዊ ሱፐርቪዥን ፕሮግራም በፌደራል፣ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች መካከል የእርስ በርስ ልምድና ተሞክሮዎች እንዲኖር ከማድረጉም ባለፈ ከተገኙት ልምድና ተሞክሮዎች በመነሳት በቀጣይ ለሚካሄደው አገራዊ የፀረ-ሙስና ትግል ላይ የጋራ ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡

ይህ የመጀመሪያው ዙር የሆነው አገርዓቀፍ የኮሚሽኖች የአቻ ለአቻ ድጋፋዊ ሱፐርቪዥን ፕሮግራም ከዚህ በኋላም በየዓመቱ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም ከዚህ ልምድ በመውሰድ የክልልና ከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች በየደረጃው ያሉ የዞን እና የክፍለ ከተማ ብሎም የወረዳ የሥነምግባር መከታታያ ክፍሎች ላይም የአቻ ለአቻ ድጋፋዊ ሱፐርቪዥን ፕሮግራሙን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

# ሳይቃጠል በቅጠል

## በተቋማት የሚስተዋለውን ሙስና እና ብልሹ አሰራር የቅድመ ሙስና መከላከል ጥናት በማካሄድ የሚባክነውን የመንግስትና የህዝብ ሀብት ማዳን ያስፈልጋል!

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በአዋጅ ከተሰጠው ተግባር መካከል በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶችና ህዝባዊ ድርጅቶች ላይ የሚስተዋለውን ሙስና እና ብልሹ አሰራር የአስቼኳይ የሙስና መከላከል ጥናት በማካሄድ የሚባክን የህዝብና የመንግስት ሀብት ማዳን ነው። ባለፉት ጊዜያትም ሊባክኑ የነበሩ በብዙ ቢሊዮን ብር የሚቆጠር የመንግስትና የህዝብ ሀብት ከመዝባሪዎች ማዳን መቻሉ ይታወቃል።

በመሆኑም የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በዕለት ደራሽ እርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት ባካሄደው የአስቼኳይ የሙስና መከላከል ጥናት ከመመሪያ ውጪ በ17.4 ሚሊዮን ብር የተካሄዳ የመኪና ሸራ ግዢ ከምዝበራ ማዳን ችሏል።

የዕለት ደራሽ እርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት በመንግሥት የልማት ድርጅትነት ተቋቁሞ በዋናነት በአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ወደተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚላኩ የእርዳታ እቃዎችን የሚያጓጉዝ የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ሲሆን፣ ድርጅቱ በ2015 ዓ.ም ለገዛቸው 100 ለሚሆኑ መኪናዎች መሸፈኛ የሚውል የፕላስቲክ ሸራ ኦኤምአር (OMR) ከተባለ ተቋም መግዛቱን ሰነዶች ያሳያሉ።

ይሁን እንጂ ድርጅቱ በመንግሥት የግዢ አዋጅ 649/2021 አንቀጽ 51 መሰረት ቀጥታ ግዢ ለመፈጸም ያስችላሉ የተባሉትን መስፈርቶች ሳያሟላ ግዢ ማከናወኑን የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በጥናት ደርሶበታል። በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ዴስክ ኃላፊ ተስፋዬ በቀለ ከኢቲቪ ጋር ባደረጉት ቆይታ፥ በተቋሙ ውስጥ የሚሰራ ግለሰብ ተደራድሮ የእቃ ግዢዎችን እንደፈፀመ ይገልፃሉ።

የዕለት ደራሽ እርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት ዋና ዳይሬክተር አማረ ደቻሳ በበኩላቸው፥ መኪናዎቹ ቶሎ ሸራ ተገዝቶላቸው በአፋጣኝ ወደ ስራ እንዲገቡ ለማስቻል ያሳለፍነው ውሳኔ ነው የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ። ግዢው አስቸኳይ ነበር ይበሉ እንጂ፣ ግዢውን ለመፈጸም 4 ወራት መውሰዱ ተገልጿል። ዋና ዳይሬክተሩ አማረ ደቻሳ በ45 ቀናት ውስጥ መኪኖቹ ይገባሉ ተብሎ የተገመተ በመሆኑ የግዢ ሂደቱ አስቀድሞ መከናወኑን፣ ነገር ግን ሸራዎቹ ተሰፍተው ቢዘጋጁም መኪኖቹ በታሰበው ጊዜ አለመድረሳቸውን ይናገራሉ።

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ግዢው ተቋርጦ ገንዘቡ ወደ መንግሥት ካዝና ይመለስ ብሎ ቢያሳስብም ድርጅቱ ግን ምክረ ሀሳቡን ተግባራዊ አለማድረጉ ተገልጿል።

የዕለት ደራሽ እርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት ዋና ዳይሬክተር "በ3 ቀናት ውስጥ ግብረ መልስ ካልሰጠናችሁ መቀጠል ትችላላችሁ" መባላቸውን በማስተባበያቸው ውስጥ ያነሳሉ። የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ዴስክ ኃላፊ ተስፋዬ በቀለ ግን "የኛን ፍቃድና ምላሽ ሳይጠብቁ ወደ እርምጃ ገብተዋል" ሲሉ ይከሳሉ። የመኪና ሸራ ሻጩ የምርቱ ብቸኛ አቅራቢ ነው የሚለው ሌላው ድርጅቱ የሚያቀርበው መከራከሪያ ሲሆን፣ ዳይሬክተሩ ስለዚህ ጉዳይ ሲያስረዱ ብቸኛ አቅራቢ ስለመሆናቸው እቃ አቅራቢዎቹ ነግረውናል ይላሉ።

የኦኤምአር ስራ አስኪያጅ ሀይማኖት በቀለ በበኩላቸው ብቸኛ አቅራቢነታችን (ወኪልነታችን) ለአንድ ድርጅት ነው፣ እሱም ቱርክ ውስጥ ያለ ድርጅት ነው፤ ይሁን እንጂ ተመሳሳይ ምርት በኢትዮጵያ ገበያ ላይ ይገኛል ብለዋል። ድርጅቱ ራሱም ኖሯቸው በዘርፉ እየተንቀሳቀሱ መሆኑንም በንግድ ሚኒስቴር የፈቃድ እና ቁጥጥር ስራ አስፈፃሚ ጂራታ ነመራ ገልጸዋል።

ኢቢሲ ባደረገው ምልከታ የዕለት ደራሽ እርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት በጥቅምት ወር 2016 ዓ.ም ከተመሳሳይ የንግድ ተቋም በ327 ሺህ ብር የመሰብሰቢያ ድንኳን ያለ ጨረታ መግዛቱን አረጋግጧል። የዕለት ደራሽ እርዳታ ትራንስፖርት ድርጅት ዋና ዳይሬክተር አማረ ደቻሳ ባነሱት የማስተባበያ ሀሳብ የንግድ ተቋሙ "የኛ እቃዎች በጥራት የተሻሉ ናቸው"

**በተካሄደው የአስቼኳይ የሙስና መከላከል ጥናት ከመመሪያ ውጪ በ17.4 ሚሊዮን ብር የተካሄዳ የመኪና ሸራ ግዢ ከምዝበራ ማዳን ችሏል።**

ከ5 ድርጅቶች የዋጋ ንጽጽር ማቅረቢያ (ፕሪፎርማ) ወስዶ የዋጋ ንጽጽር ያደረገ ሲሆን፣ የተጠቀሰው የምርቱ አቅራቢ ድርጅትም ብቸኛ አለመሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። ይህም ድርጅቱ ከመመሪያ ውጪ በ17.4 ሚሊዮን ብር የመኪና ሸራ ግዢ መፈፀሙን ያመላክታል።

ፕላስቲክ እና ከፕላስቲክ የተሰሩ እቃዎችን የሚያስመጡ ከ4 ሺህ 500 በላይ ነጋዴዎች የጸና ንግድ ፍቃድ ማለቱን ተከትሎ የድርጅቱ የግዢ ክፍል ግዢውን ስለመፈፀሙ ይናገራሉ።

ድንኳኑም መሰብሰቢያ እና ማረፊያ በመታጣቱ በአስቸኳይ እንዲገዛ ተደርጓል ይባል እንጂ፣ አሁን ላይ የሚወገዱ እቃዎች ማከማቻ ክፍል እንደሚገኝ ኢቢሲ ተመልክቷል።

# ከሙስና ምርመራ ማህደር

በዚህ አምድ የተለያዩ ከሙስና እና ብልሹ አሠራር ጋር በተያያዘ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከናወኑና ለህብረተሰቡ ከፍተኛ እውቀትና እውነተኛ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የሚታመኑና በሙስና ወንጀል የተመዘበረ የሀገር፣ የህዝብና የመንግስት ሀብት በማስመለስ ዙሪያ የተከናወኑ ተግባራት እና ግንዛቤ የሚፈጥሩ ዋና ዋና ጉዳዮች አጠር ተደርገው የሚቀርቡበት ነው፡፡

በመሆኑም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ጊዜ ቀጠሮ ችሎት በከባድ የሙስና ወንጀል የተጠረጠሩት የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንትን ጨምሮ በ6 ግለሰቦች ላይ የ15 ቀን ክስ የመመስረቻ ጊዜ ፈቅዷል፡፡ ጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን የክስ መመስረቻ ጥያቄንና የተጠርጣሪ ጠበቆችን የመከራከሪያ ነጥብ ተመልክቷል፡፡

ተጠርጣሪዎቹ 1ኛ የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ሀብታሙ አበበ አጊሾ (ዶ/ር)፣ የዩኒቨርሲቲው አካዳሚና ምርምር ዘርፍ ምክትል ፕሬዚዳንት ታምራት ታገሰ ተኮራ (ዶ/ር)፣ 3ኛ ኮንትራክተር የሆነው ደሳለኝ አስረዳ፣ 4ኛ የዩኒቨርሲቲው የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ኃላፊ ሙላቱ ኤርትሮ ጡንዳዳ፣ 5ኛ የዩኒቨርሲቲው የፋይናንስ ዳይሬክተር ማርቆስ ዮሃንስ ረገዮ እና የቀድሞ የአዋሽ ባንክ ሆሳህና ቅርጫፍ ስራ አስኪያጅ የነበረው መለሰ ግርማ ኤርጋኖ ናቸው፡፡

የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ደቡብ ቅርጫፍ መርማሪ የምርመራ ስራውን አጠናቆ የምርመራ መዝገቡን ለዐቃቤ ሕግ ማስረከቡን ለጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ አስታውቋል፡፡ ከዚህም በኋላ የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዐቃቤ ሕግ በመዝገቡ ላይ ተሰይሞ ተጠርጣሪዎች የተጠረጠሩበትን መነሻ ጉዳይ በዝርዝር ለጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ አቅርቦ የ15 ቀን ክስ መመስረቻ ጊዜ እንዲፈቀድለት ጠይቋል፡፡

በዚህም ተጠርጣሪዎቹ በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ለንግስት ኢሌኒ መታሰቢያ ሆስፒታል የኦክስጂን ማምረቻ ለማስገንባት መቀመጫውና ዋና መስሪያ ቤቱን ካናዳ ቶሮንቶ ካደረገ ኤ.ኤ.ኤም.ኢዲ ቴክኖሎጂ ኢንካ ለተባለ ድርጅት የመንግስትን የግዢ መመሪያው ባልጠበቀ መንገድ በአምስት አመት አፈጻጸሙ እየታየ መከፈል የሚገባውን አሰራር በመተላለፍ በውል ላይ የተዘረዘሩ ስራዎች ሙሉ በሙሉ ባልተሰሩበት ሁኔታ ለድርጅቱ የ57 ሚሊየን 383 ሺህ 956 ብር ከ72 ሳንቲም ለታለመለት አላማ ሳይውል በመክፈል ጉዳት እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

በተለይም የውል ማስከበሪያ የውሉን ጠቅላል ዋጋ 10 ከመቶ ማለትም 117 ሚሊየን 10 ሺህ 859 ብር ከ60 ሳንቲም የውል ማስከበሪያ ሳይቀርብ እና ስራውም በውል ላይ በተገለጸው ጊዜ ሳይጠናቀቅ በመቅረቱ ይህ የውል ማስከበሪያ ዋስትና ቀርቦ ቢሆን ኖሮ ለመንግስት ገቢ መደረግ የነበረበትን ጥቅም አሳጥተዋል በሚል የተጠረጠሩበትን ወንጀል ዐቃቤ ሕግ በክስ መመስረቻው ላይ በዝርዝር አቅርቧል፡፡

በተጨማሪም ደሳለኝ አስረደ የግንባታ ስራ ተቋራጭ ደግሞ የመምህራን መኖሪያ ቤት 2 ህንጻ ግንባታ ስራ ግንቦት 2013 ዓ.ም እና ጥር ወር 2016 ዓ.ም በተገባው ውል መሰረት ለዚሁ ህንፃ ተቋራጭ በተጋነነ ዋጋ በመስጠት 272 ሚሊየን 170 ሺህ 210 ብር ከ60 ሳንቲም ያለአግባብ ለተጨማሪ የግንባታ ወጪ መደረጉ፤ ክፍያ በመፈጸም በዚህ ልክ በመንግስት ላይ ጉዳት በማድረስ እና ለውለታ 26 ሚሊዮን ብር ጥቅም ማስገኘትና ማግኘት የሚል የጥርጣሬ መነሻም በዐቃቤ ሕግ በኩል ቀርቧል፡፡

እንዲሁም በዝምድና እና በትውውቅ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ባለቤት እህት እና ሌሎች ሁለት ሰራተኞች ባልሰሩት ስራ በአበል መልክ የዩኒቨርሲቲውን ገንዘብ ያለአግባብ በመመዝበር ከ6 ሚሊየን ብር በላይ ጉዳት የደረሰ መሆኑን ዐቃቤ ሕግ ጠቅሷል፡፡ ተጠርጣሪዎች ከሌሎች እጃቸው ለጊዜው ካልተያዙ ተጠርጣሪዎች ጋር በመመሳጠር በመንግስት ላይ 487 ሚሊየን 333 ሺህ 912 ብር ከ78 ሳንቲም ጉዳት እንዲደርስና ለሌሎች ያልተገባ ጥቅም እንዲያገኙ የተደረገ መሆኑን ጠቅሶ ስልጣንን ያለአግባብ መገልገል የሙስና ወንጀል የተጣራባቸውና የምርመራ መዝገቡን ነሐሴ 12 ቀን 2016 ዓ.ም ከመርማሪ ፖሊስ እንደደረሰው ለችሎቱ አቅርቧል፡፡

የምርመራ መዝገቡ ውስብስብ መሆኑን የጠቀሰው ዐቃቤ ሕግ መዝገቡን በጥልቀት መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት ሰፋ ያለ ጊዜ እንደሚያስፈልገው ገልጾ በተመሳሳይ ወንጀል የተጠረጠሩ ሌሎች ተጠርጣሪዎች ያሉ እና ጉዳያቸው በአንድ መዝገብ የተጣራ በመሆኑ በአንድ ላይ ክስ ለማዘጋጀት በወ/መ/ስ/ስ /109 /1 መሰረት የ15 ቀን የክስ መመስረቻ ጊዜ እንዲሰጠው ጠይቋል፡፡ የተጠርጣሪ ጠበቆች በበኩላቸው በዐቃቤ ሕግ የቀረበው ዝርዝር የጥርጣሬ መነሻ ተጠርጣሪዎቹ የተሳትፎ ደረጃ ያልቀረበበትና በጥቅል ወንጀል ተፈጽሟል ተብሎ በደፈናው ክስ መመስረቻ ጥያቄ ሊቀርብ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

በዋናነት ዐቃቤ ሕግ ምርመራውን ሲመራ ቆይቶ እንደ አዲስ “የምርመራ መዝገቡን ተመልክቼ ለመወሰን እንድችል” ክስ የመመስረቻ ጊዜ ይፈቀድልኝ ማለቱ አግባብ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በተመሳሳይ ከአበል የወንጀል ተግባር ጋር በተያያዘ ሌሎች በዋስ በተለቀቁበት ሁኔታ ላይ ከወንጀል ድርጊቱ ጋር የማይገናኙ ደንበኞቻችን በእስር እንዲቆዩ ተደርጎ የክስ መመስረቻ መጠየቁ ተገቢነት የለውም በማለት የተከራከሩ ጠበቆችም ነበሩ፡፡ በጥቅሉ ደንበኞቻቸው ቋሚ አድራሻ ያላቸውና በየትኛውም ጊዜ ቢጠሩ መቅረብ የሚችሉ መሆናቸውን ጠቅሰው ዋስትና እንዲፈቀድላቸው ተጠይቋል፡፡

ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ የመመርመር ስልጣን ያለው ፖሊስ መሆኑን በመጥቀስ፣ ምርመራ መምራት ማለት የህግ ድጋፍ መስጠት ማለት መሆኑን ገልጾ መልስ ሰጥቷል፡፡ ዐቃቤ ሕግ ተፈጽሟል ባለው የወንጀል ተግባር ጥቅም የተገኘበትና በመንግስት ላይ ከፍ ያለ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን በመግለጽ የተጠረጠሩበት ወንጀል የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 መሰረት በከባድ ማለትም ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ በሚችል ድንጋጌ ስር ሊያስከስስ እንደሚችል ጠቅሶ የዋስትና ጥያቄውን በመቃወም ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኝ ክርክሩን የመረመረው የጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ ነሃሴ 9/2016 ዓ.ም ረፋድ ላይ ለክስ መመስረቻ ጊዜ መፍቀድ ተገቢ መሆኑን ገልጾ የተጠርጣሪዎችን ዋስትና በማለፍ ለዐቃቤ ሕግ የ15 ቀን የክስ መመስረቻ ጊዜ ፈቅዷል፡፡

በሌላ የሙስና ወንጀል መረጃ በሀሰተኛ ማንነት የፍርድ ቤት የወራሽነት ማረጋገጫ አቅርበው ከግለሰብ የባንክ ሂሳብ 28 ሚሊየን ብር ሊመዘብሩ ነበር የተባሉ ግለሰቦች ላይ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ተረኛ ወንጀል ችሎት ክስ ቀርቧል፡፡ የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ሕግ በሶስት ተከሳሾች ላይ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ ቁጥር አንቀጽ 32 ንዑስ ቁጥር 1 (ሀ) እና የሙስና ወንጀሎች ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 32 ንዑስ ቁጥር 1፣ 2 እና 3 ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል በማለት የተሳትፎ ደረጃቸውን ጠቅሶ ክስ አቅርቦባቸዋል፡፡

ተከሳሾቹ 1ኛ ዳዊት አይዳኙህም አጎናፍር፣ 2ኛ እስራኤል ወልዴ ድንቁ፣ 3ኛ የቅሊንጦ አካባቢ ፖሊስ ጣቢያ አባል የነበረ ኮንስታብል ሀብታሙ ተመስገን ናቸው፡፡ ተከሳሾች ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለራሳቸው ለማግኘት በማሰብ ማንነታቸውን በመሰወር በተለይም 1ኛ ተከሳሽ ነዋሪነቱ በአዳማ ከተማ ሆኖ እያለ ማንነቱን በመቀየር አፋር ክልል ገቢረሱ ዞን በገለአሎ ወረዳ ገፍራም 2 ቀበሌ ነዋሪ ሳይሆን ነዋሪ ነኝ በማለት የሟች አድማሱ ምህረቱ ልጅም ሆነ ወራሽ ባልሆነበት ሁኔታ ወራሽ እንደሆነ በማስመሰል “አብነት አድማሱ ምህረቱ” ስም በተጭበረበረ መንገድ የነዋሪነት መታወቂያ ማውጣቱን ዐቃቤ ሕግ በክሱ ላይ አስፍሯል፡፡

በዚህ መልኩ በተጭበረበረ ስምና መታወቂያ አፋር ክልል ገቢረሱ ዞን በገለአሎ ወረዳ ፍርድ ቤት በመጋቢት 5 ቀን 2016 ዓ.ም የአቶ አድማሱ ምህረቱ ወራሽ እንደሆነ በማስመሰል የፍርድ ቤት የወራሽነት ማረጋገጫ ማውጣቱ በክሱ ዝርዝር ላይ ተገልጿል፡፡

2ኛ ተከሳሽም የተከሳሽ “አብነት አድማሱ” ስም በተጨበረበረ መንገድ የወጣ መታወቂያ በመጠቀበም የፍርድ ቤት የወራሽነት ማረጋገጫ እንዲወጣለት በማድረግ 1ኛ እና 3ኛ ተከሳሾችን ከአዳማ ከተማ ወደ አዲስ አባባ ጉዞውን በማመቻቸት 3ኛ ተከሳሽ ፖሊሳዊ የደንብ ልብስ በመልበስ ከ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ጋር በመሆን መጋቢት 18 ቀን 2016 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ ልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲስ አበባ ቅርንጫፍ ከሟች አድማሱ ምህረቱ 28 ሚሊየን ብር ለማውጣት ከ2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጋር በአካል ቀርቦ እንደነበርና የባንኩን እምነት ለማግኘት እና ክፍያ እንዲፈፀምላቸው 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች የንግድ ባንክ ሰራተኞችን ለወራሽ ገንዘቡን አስተላልፉለት በማለት የንግድ ባንክ ደንበኛ ከነበሩት ከሟች አድማሱ ምህረቱ 28 ሚሊየን ብር ወደ 1ኛ ተከሳሽ ሂሳብ ሊያተላለፉ ሲሉ የተያዙ መሆናቸውን ተጠቅሷል፡፡

በዚህም በዋና ወንጀል አድራጊነት በህዝብ አስተዳደርና አገልግሎት ላይ በሚፈፀም ከባድ ማታለል የሙስና ወንጀል ተከሰዋል፡፡ ተከሳሾቹ ነሃሴ 9/2016 ዓ.ም በተረኛ ችሎት ቀርበው ችሎቱ ማንነታቸውን በማረጋገጥ የክሱ ዝርዝር እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ ተከሳሾቹም የቀረበባቸው ክስ ላይ የዋስትና መብታቸው እንዲከበር ፍርድ ቤቱን የጠየቁ ሲሆን÷ ከሳሽ ዐቃቤ ሕግ ተከሳሾቹ ዋስትና በሚያስከለክል ድንጋጌ ስር መከሰሳቸውን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ ችሎቱ የግራ ቀኝ ክርክሩን መርምሮ የተከሳሾችን የተከሰሱበት ድንጋጌ ዋስትና በሚያስከለክል ድንጋጌ ስር መሆኑን ጠቅሶ የዋስትና ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ በማረሚያ ቤት ሆነው እንዲከታተሉ ትዕዛዝ በመስጠት ለጥቅምት 4 ቀን 2017 ዓ.ም ቀጥሯል፡፡

# መልካም ዜጋ

## በጥቂት የታመነ በብዙ ይሾማል

አሜሪካን ካንሳስ ሲቲ ነዋሪ የሆነችው ሳራ ዳርሊንግ ከስራ ወጥታ ወደ መኖሪያ ቤቷ በማቅናት ላይ ሳለች አንድ በዕድሜ ጠና ያሉ አዛውንት ከመንገድ ዳር ቁጭ ብለው ሲለምኑ ተመለከተች፡፡ ሳራ ወደ አዛውንቱ በመጠጋት ቦርሳዋን ከፍታ የተወሰኑ ዶላሮችን ሰውየው ከጎናቸው ባስቀመጡት የፕላስቲክ ኩባያ ውስጥ አኑራ ጉዞዋን ቀጠለች፡፡

ሳራ ከምንግዜውም በላይ በህይወቷ ደስተኛ ነበረች፤ ከምትወደውና ከምታፈቅረው ጓደኛዋ ጋር በትዳር ለመጣመር የቀናት ዕድሜ ቀርቷቸዋል፡፡ ለእርሷ ከፍተኛ ክብርና ፍቅር ያለው ፍቅረኛዋ እጅግ ውድ የሆነ ዳይመንድና የቃል ኪዳን ቀለበት ገዝቶ በጉልበቱ ተንበርክኮ የታገቢኛለሽ ጥያቄ ካቀረበላት እና በደስታ እሺ ካለችው ጊዜ አንስቶ ህይወቷ በሀሴት ተሞልቷል፡፡ ምሽት ላይ እንደተለመደው በስስት የምትወደውን የዳይመንድ ቀለበት አይታ ለመተኛት ቦርሳዋን ከፈተችው በድንጋጤ ደርቃ ቀረች፣ ቀለበቱ በቦታው አልነበረም፡፡ ቦርሳዋን የከፈተችው መንገድ ዳር ቁጭ ብለው ለሚለምኑት አዛውንት ገንዘብ ለመስጠት ብቻ እንደነበር ትዝ ሲላት የሰውየው ገንዘብ መሰብሰቢያ ኩባያ ውስጥ ቀለበቱን አብራ ማኖሯን አስታወሰች፡፡

ለእጮኛዋ ስልክ በመደወል ሁኔታውን አጫወተችው፣ እጮኛዋም እየበረረ መጥቶ ተያይዘው በልመና ወደ ሚተዳደሩት ሽማግሌ ሄዱ፡፡

ሰውየው በቦታው አልነበሩም "በእርግጥ ውድ የሆነ ቀለበት አግኝተው እንዴት ተመልሰው በቦታው ሊቀመጡ ይችላሉ" የእጮኛዋ ግምት ነበር፡፡ በቀጣዩ ቀንም በድጋሚ ከእጮኛዋ ጋር ሽማግሌውተቀምጠው ወደሚለምኑበት ቦታ ሄዱ፤ አሁንም ሰውየው በዚያ ስፍራ አልነበሩም፡፡ "በቃ ጦስሽን ይውሰድ ከእንግዲህ እርምሽን አውጪ" አላት እጮኛዋ፡፡

በሶስተኛው ቀንም ሳራ ለእጮኛዋ ደውላ ወደ ሽማግሌው ቦታ እንዲሄዱ ጠየቀችው፤ እጮኛዋም በመገረም "ስድስት ሺህ ዶላር የሚያወጣ ቀለበት ችግረኛ እና በረንዳ የሚያድር ሰው እጅ ገብቶ አገኝዋለሁ ብለሽ እንዴት ታስቢያለሽ?" ነበር ያላት ...! ሳራም "በቃ የዛሬን ብቻ እንያቸው፣ ሰውየው ከሌሉ እርሜን አወጣለሁ" አለችው፡፡ እጮኛዋም የሳራን ፍላጎት ለማሟላት ብቻ ተስማምቶ ጉዞዋቸውን አቀኑ፤ ሽማግሌው በቦታው ተቀምጠው ሲለምኑ አገኟቸው፡፡ ሳራ በደስታ ተዋጠች፤ አላውቅሽም ብለው እንዳይሸመጥጡ የሚል ስጋት እንደገባት ወደ ሽማግሌው ተጠጋች፡፡ "አባት ያስታውሱኛል?" በማለት ጠየቀች… ሽማግሌው ቢል ሬይ ቀና ብለው ተመልክተዋት "አላወቅኩሽም ልጄ" ሲሉ መለሱላት፡፡ ሳራም "ከሶስት ቀን በፊት ከቦርሳዬ ገንዘብ አውጥቼ ኩባያዎ ዉስጥ ሳስቀምጥ ሌላ ዕቃ አብሬ አኑሬ ነበር" ስትላቸው… "የጣት ቀለበት ነው?"አሏት… "አዎን አባት"! ሽማግሌው ቢል ቀለበቱን ጠቅልለው ካስቀመጡበት ኪስ በማውጣት "አንድ ቀን እንደምትመለሺ አውቅ ነበር" በማለት ቀለበቱን ከሰጧት በኋላ ... ቀለበቱን ያገኘሁት ዕለት ትክክለኛ ወይም አርቴፊሻል ቀለበት መሆኑን ለማወቅ ወደ ጌጣጌጥ ሱቅ ወስጄው ነበር፤ እነሱም ትክክለኛ መሆኑን ነግረውኝ 4,000 ዶላር ሊገዙኝ ጠይቀውኝ ነበር፡፡"

"በእርግጥ ኑሮውን በበረንዳ ለሚያሳልፍና በልመና ለሚተዳደር ሰው 4 ሺህ ዶላር ከፍተኛ ገንዘብ ነው፤ ነገር ግን እኔን ለመርዳት ብላ በስህተት ቀለበት የጣለችን ሴት ንብረት መንካት አልፈለኩም፡፡ በመሆኑም በጥንቃቄ አኑሬው የአንቺን መምጣት ስጠባበቅ ነበር፡፡" ሲሉ መለሱላት፡፡

ሳራ ዳርሊንግ እና እጮኛዋ የመልካሙን ቢል ሬይ ታሪክ ከታች ቀለበቷን ሲሰጣት ከሚታየው ምስል ጋር በማያያዝ በሶሻል ሚዲያ (Facebook) ላይ ለቀቁት፡፡

